መ/ቁ 33244

ቀን 27/06/2016 ዓ/ም

ዳኛ አብርሃም ሙሴ

ከሳሽ:- ቁም ለአከባቢ (Defend the environment)

ተከሳሽ፦ሀዋስ ከተማ ኮንስትራክሽን እና ከተማ ልማት መምሪያ

መዝገቡ የተቀጠረዉ ጉዳዩ ታይቶ ዉሳኔ ለመስጠት ሲሆን በዚዉ መሠረት ፍርድ ቤቱ የሚከተለዉን ዉሳኔ ሰጥተዋል።

## ፍርድ

መዝገቡ አከባቢ በመበከሉ ምክንያት ጉዳት እየደረሰ ይገኛል በማለት የቀረበ ሲሆን ከሳሽ በቀን 11/04/2016 ዓ/ም በጽሁፍ ባቀረበዉ አቤቱታ መነሻ በተከሳሽ በሀዋስ ከተማ ኮንስትራክሽን እና ከተማ ልማት መምሪያ በበላይነት በሥሩ የሚያስተዳድረዉን ሀዋሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ቄራ አገልግሎት በሀዋሳ ከተማ ታቦር ክፍለ ከተማ ፋራ ቀበሌ ዉስጥ የሚገኘዉን ቄራ አሁን በሚገኝበት ቦታ ለዓመታት ለሀዋሳ ከተማ እና በዙሪያዉ የሚገኙ ማህበረሰብ ክፍሎች ቄራ አገልግሎት ማለትም በየእለቱ ብዙ የእርድ እንስሳትን በማረድ ሥጋ እና ለሎች የቄራ አገልግሎት የሚያቀርብ ተቋም በመሆኑ ከሚሰጠዉ አገልግሎት የተነሳ ብዙ የእርድ ተረፈ ምርቶችን ማለትም ደም፣ ቁርጥራጭ ሥጋ፣ አጥንት እና ሌሎች አከባቢ የሚበክሉ ተረፈ ምርቶችን በተገቢዉ ሁኔታ የማያስወግድና የማያስተዳድር

በመሆኑ አከባቢዉን በተለየ መልኩ አየር፣አፈር እና ውሃዉን እየበከለ ይገኛል። በዚህ ሁኔታ በአከባቢዉ ብክለት እየተፈጠረ የቄራ አገልግሎት በሚሰጥበት አከባቢ ላይ ለሚኖሩ ለብዙ ነዋሪዎች እና መንገዱ በሚመላለሱ ሰዎች ጤና ላይ፣ ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎቻቸዉ ላይ ከፍተኛ ችግር እያደረሰባቸዉ ያለ በመሆኑ የማህበረሰቡን ማመልከቻ መነሻ በማድረግ በተሰባሰበዉ መረጃ መሠረት የከሳሽ ተቋም የበጎ አድራጎት ባለሙያዎች በቦታዉ በመገኘት ባደረጉት በሥራ ምልከታ አረጋግጠዋል። በመሆኑ ተከሳሽ በአከባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 አንቀጽ 3 መሠረት "ማንኛዉም ሰዉ አስፈላጊዉን እና በአከባቢዉ ከመጠን በላይ አከባቢዉ እንዲበከል ወይም በሌሎች ሰዎች አማካኝነት እንዲበከል

እንዲያደርግ አይፈቀድለትም"። በማለት በህጉ ከተደነገገዉ ድንጋጌ ጋር በሚጋጭ መልኩ ያለዉን ሀላፊነት በአግባቡ ባለመወጣት አከባቢን በመበከል የቄራ አገልግሎት በሚሰጥበት ዙሪያ በሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍል እንዲሁም በዛዉ ለሚያልፉ መንገደኞች በኢ/ፌ/ዴ/ሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 44 (1) መሠረት እና ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ባላቸዉ ሀገራችን አጽድቃ በተቀበለቻቸዉ አለም አቀፍ የሰብዓዊ አከባቢያዊ መብቶች ስምምነቶች መሠረት ንጹህ እና ጤንነቱን በተጠበቀ አከባቢ የመኖር መብታቸዉን እየጣሰ ይገኛል።

ከሳሽ በተከሳሽ አላስፈላጊ የሆነዉን በአከባቢዉ ላይ እየተፈጠረ ያለዉን ብክለት በተመለከተ አስፈላጊዉን ምርመራ አድርጎ ዉጤቱን እንዲገልጽለት ለኢ/ፌ/ዲ/ሪ የአከባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ጥቅምት 29/2016 ዓ/ም የደብዳቤ ቁጥር ቁለአ/0011/16 በጻፈዉ ደብዳቤ የድጋፍ ጥያቄ አቅርቧል። ሥልጣን ያለዉ መሥሪያ ቤትም ጥቅምት 29/2016 ዓ/ም የደብዳቤ ቁጥር 12/3.1/92003/15 በሆነዉ በተሰጠዉ መልስ በተከሳሽ ድርጊት ከፍተኛ የአከባቢ ብክለት ተፈጥሮ ለአከባቢዉም እንዲሁም በሰዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ እንዳለ በማረጋገጥ በሲ/ብ/ክ/መ የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር የተበከለዉን አከባቢ ንጽሁ የማድረግ እቅድ በማዘጋጀት እርምጃ እንዲወስድ ለክልሉ እና ለከተማዉ አስተዳደር የአከባቢ ደን እና የአየር ንብረት ለዉጥ ባለሥልጣን የከተማ አሰተዳደሩ በሚያወጣዉ ዕቅድ አፈጻጸም ላይ ክትትል እንዲያደርግ ከሳሽም ጉዳዩ በፍርድ ቤት እንዲከታተል ይሁን በማለት እሱንም በግልባጭ ከላይ ባመለከትነዉ ተቋማት ለሁሉም በአድራሻዎቻቸዉ በትክክል ግልባጭ ተልኮላቸዋል። ተከሳሽ ተቋም በተሰጣቸዉ ማስጠንቀቂያ መሠረት አስፈላጊዉን እርምጃ ለመዉሰድ አከባቢዉን ለመጠበቅ ያልሰሩ በመሆናቸዉ ከሳሽ ጥቅምት 21/2016 ዓ/ም በደብዳቤ ቁጥር DTE 017116 በሆነዉ በጻፈዉ አቤቱታ ሲ/ብ/ክ/መ አከባቢ ደን እና የአየረ ለዉጥ ባለሥልጣን በአዋጁ በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት በተከሳሽ ላይ አስፈላጊዉን አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ የጠየቀ ቢሆንም መሥሪያ ቤቱ የከሳሽን አቤቱታ ከመቀበል ባሻገር ምንም አይነት እርምጃ ያልወሰደ በመሆኑ ፍርድ ቤት አስፈላጊዉን ምርመራ በማድረግ ዉሳኔ እንሰጥ በማለት ከሳሽ ይህን ክስ በዚ ችሎት አቅርበዋል።

በሌላ በኩል ይህ ፍርድ ቤትም የከሳሽን አቤቱታ ከተቀበለ በኃላ የተከሳሽን መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በመያዝ መጥሪያ ልኳል። ይሁን እንጅ ተከሳሽ አልቀረቡም። በተደጋጋም መጥሪያ ቢላክም ሊቀረብ አልቻለም። ከዚህ በኂላ ፍርድ ቤቱም ተከሳሽ በሌሉበት የከሳሽ አቤቱታ ሰምቶ ተከሳሽ በመንግስት ሥር የሚተዳደረዉን የቄራ አገልግሎት ድርጅት የሚወጣሁን የእንስሳቱ

የተረፈ ምርት ቆሻሻ ከተከሳሽ ተቋም ዉስጥ የሚወጣዉ የነዋሪዎች ወይም የአከባቢ ህዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረስ ነዉ? አይደለም? እንዲሁም በአከባቢ ሰዎች ላይ ጉዳት እያደረሰ ያለ ከሆነ የተከሳሽ ተቋም መምሪያ አካባቢዉን ማጽዳት አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለዉን እንደጭብጥ ተይዘዋል፡፡ ከዛ በኃላ ፍርድ ቤትም ከሳሽ ያቀረበዉን ማስረጃ የተለያዩ የሰነድ ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተከሳሽ በለሉበት የከሳሽ ክስ ከሰማ በኃላ የሚከተለዉን ዉሳኔ ሰጥተዋል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

- ከተከሳሽ ከቄራ አገልግሎት የሚወጣዉን የተለያዩ በሰዎች ጤና ላይ ጉዳት እያደረሰ አከባቢዉን የምበክል ድርጊት እንዲቆም ብለን ወስነናል፡፡
- የከሳሽ የወጭ እና ኪሳራ የመጠየቅ መብቱ ተጠብቆለታል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- ይግባኝ መጠየቅ መብት ነዉ፡፡
- ምዝገቡ ተዘግቷል መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡